የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
የዋሽንግተን ዲሲ እና አካባቢው
ሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤት

The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Archdiocese of Washington DC
and its surroundings.

መስከረም ፩ ቀን፡፳፻፪ ዓ.ም

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ፡**

**አሜን።**

በአለንበት ሀገር በሰሜን አሜሪካ፤ በሀገራችን በኢትዮጵያ እና በልዩ ልዩ አኅጉራት የምትገኙ ወገኖቼ!

ከሁሉ አስቀድሞ የዘመናት ባለቤት አምላካችን እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁንና እንኳን ከዘመነ ማቴዎስ ወደዘመነ ማርቆስ በሰላም አደረሳችሁ እያልኩ ዘመኑ የሰላምና የጤና የእዉቀትና የሥራ ዘመን እንዲሆንላችሁ መልካም ምኞቴን በዋሽንግተን ዲሲ እና አካባቢው ሀገረ ስብከት ስም በታላቅ ትኅትና እየገለጽኩ ቸርነቱንና ምሕረቱን ከእኛ ያላራቀ በዕድሜአችን ላይ ተጨማሪ ዕድሜ አድርጎ በሰጠን ዓውደ ዓመት ልንጠቀምበት የሚገባንን መልእክት እንደሚከተለው ሳቀርብ በታላቅ ትህትና ነው።

**“ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከክርስቶስ ኢየሱስም ከጌታችን ጸጋና ምሕረት ሰላምም ይሁን”**

፩ ጢሞ ፩፡፪-

የተከበራችሁ አባቶቼና እናቶቼ ወንድሞቼና እኅቶቼ በአጠቃላይ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቼ!

ከማንኛውም ነገር በላይ ለሰው ልጅ ትልቁ ሀብት ሰላም የሰፈነበት ፍቅር የነገሠበት ዘመን ገጥሞት መኖር ሲችል ፡ አለ ይኖራል ማለት ይቻላል። ከዚህ ውጭ ለሰው ልጅ ሁሉም ነገር ቢኖረው የሩቅ ተመልካች ካልሆነ በስተቀር ተጠቃሚነቱ አጠራጣሪ ነው።እንደ አበው ብሂልም “ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል”ያሰኛል። ለዚህም ነበር አባቶቻችን እና እናቶቻችን የሰላምን ዘመን የምሕረትን ዓመት በመናፈቅ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ወደፈጣሪያቸው የጮሁት ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኵነኔ አክትሞ ዓመተ ምሕረት ዓመተ ሥጋዌ ተቆጥሮ የምሥራቹን ለመስማትና ለማየትም ነበር የተመኙት። ምንም እንኳ ዓመተ ምሕረት አንድ ተብሎ የሚቆጠርበት ዘመን ከአሉበት ዘመን የራቀ ቢሆንም የራቀውን አቅርቦ የረቀቀውን አጕልቶ ነቢዩ ዳዊት **“በማለዳ ምሕረትህን እንጠግባለን በዘመናችን ሁሉ ደስ ይለናል ሐሤትም እናደርጋለን”** አለ። መዝ ፺፡፲፬ _ ይሁን እንጅ እንደ ምኞታቸው ሁሉም “ጸጋና ምሕረት ሰላምም ይሁን”የሚለውን አዋጅ ለመስማትና የሰላሙንም መሪ ለማየት ሐሤትና ደስታ በሆነበት ዘመን ለመኖር አልታደሉም ምክንያቱም አረፍተ ዘመን ገቶአቸዋልና ። በአንጻሩ ግን ጸሎታቸውና ልመናቸው ቅድመ እግዚአብሔር ደርሶ ለዘመናት በተስፋ የተጠባበቁት የምሕረትና የይቅርታ ዓመት ለእኛ ለልጆቻቸው ታወጀ።ዓመተ ምሕረትም አንድ ተብሎ ተቆጥሮ እነሆ ፳፻፪ዓ.ም ደረስን።

**በዓለም ዙሪያ ያላችሁ በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኛችሁ ወገኖቼ !**

ከሰላምና ከፍቅር ከበጎ ምግባር ተራቍቶ እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሰን አደረሳችሁ መባባሉ ብቻውን ትርጉም አይሰጥም።ከዓመት ወደዓመት የመሸጋገሩ ትርጉም እንደ ቅዱስ መጽሐፍ ትምህርት **“እየጸለያችሁ ወደዘለዓለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሕረት ስትጠባበቁ ለእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ”**።ሐዋርያው ይሁዳ ቍ ፳፩ ራስን መጠበቅ ማለት ከክፉ ነገር መራቅ ክፉ አለመሥራት ከክፉ ጋር አለመተባበር በክፉዎች ምክር አለመጠመድ እና የመሳሰሉት ሲሆኑ፤ በአንጻሩ ደግሞ እውነትን አጥብቆ መፈልግ ከእውነት ጋር መኖር የፍቅር የሰላም ሰው መሆን ራስን በምግባር

ስልክ/Telephone: 703-360-0105 www.eotcdc.org ፋክስ/Fax: 703-780-0850
አድራሻ/Address: 4210 Corcoran St. Alexandria, VA 22309 ወይም/or P.O. Box 77363 Washington, DC 20013-7363

በሃይማኖት ማነጽ ወገንን መውደድ ይቅር ባይ መሆን የክርስቲያኖቸ መንፈሳዊ ግዴታ ነው።ይህን ስናደርግም ጸጋና ምሕረት ሰላምም ይሁን የሚለው ቃል ተግባራዊ ይሆናል። ዘመናትን ለፍጥረታቱ የሰጠ የዘመናት ባለቤት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ትምህርቱ ክርስቲያኖች ከማንኛውም በፊት ማድረግ ስለአለብን እና ስለሚጠበቅብን እንዲህ ሲል አስተምሮናል። <u>“ነገር ግን ሔዳችሁ ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም ያለው ምን እንደሆነ ተማሩ”</u>ማቴ፱፡፲፫፡ በተጨማሪም <u>“ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም ያለው ምን እንደሆነ ብታውቁስ ኃጢአት የሌለባቸውን ባልኮነናችሁ ነበረ”</u>ማቴ ፲፪፡፯-ሲል በማይለወጥና በማይሻር ቃሉ ተናግሮአል። በእርግጥም የክርስትና ተግባር መወነጃጀል አይደለም።ለክርስትና፤ ጉልበትና ስም ማጥፋት አድመኝነት እና ቅንዓት አስፈላጊ አይደሉም። በክርስቶስ ክርስቲያን የተባልን እና በስሙ የተጠራን ሁሉ ፈቃደ እግዚአብሔርን ፈጽመን ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ጠብቀን በፍቅረ ቢጽና በፍቅረ እግዚአብሔር ጎልብተን ሰላማዊ ኖሮ የምንኖርበትን ዓመት በብሩህ ተስፋ መቀበል የክርስትናችን ተግባር ነውና።ከዚህም በመነሳት መስዋዕቱን ከማቅረባችን በፊት ሁላችን ልናዳርገው የሚገባን ነገር ቢኖር መበደላችን ተረጋግጦ ይቅርና ብንበደል እንኳ ይቅር ባይነትን ከቃልና ከልማድ አልፈን በተግባር ልንተረጉመው ግድ ይላል።ይህን የማናደርግ ክርስቲያኖች ብንኖር ደግሞ መሳዮች እንባል ካልሆነ በስተቀር ክርስቲያኖች አያሰኝንም።መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ሲል አስጠንቅቋልና። <u>“ፍርድንና ምሕረትን ታማኝነትንም በሕግ ያለውን ዋና ነገር ስለምትተው ወዮላችሁ”ማቴ ፳፫፡ ፳፫፡</u>

## <u>ወገኖቼ!</u>

ብዙ ጊዜ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በድፍረትም ይሁን በስህተት ከሰው ልጆች ጥፋት አይታጣም ይሁን እንጂ ማንኛውም ሰው ከአፈርኩ አይመልሰኝ በሚል ፈሊጥ ከጥፋት ወደጥፋት መሽጋገር የለበትም በተሰጥው የንስሐ ዘመን ተጥቅሞ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ይቻላልና።ይህንንም በማስመልከት ቅ/ጳውሎስ እንዲህ ይላል። <u>“አስቀድሞ ተሳዳቢና አሳዳጅ አንገላችም ምንም ብሆን ይህን አደረገልኝ ነገር ግን ሳላውቅ ባለማመን ስለአደረግሁት ምሕረትን አገኘሁ”</u>።፩ጢሞ ፩፡፲፫ ሐዋርያው ከጥፋት ወደ ላማት ካለማመን ወደማመን ከጥርጥር ወደ አምልኮት ከሞት ወደሕይዎት የመመለስ ምሳሌነቱንም ሲአረጋግጥ <u>“ስለዚህ ግን የዘለዓለምን ሕይወት ለማግኘት በርሱ ያምኑ ዘንድ ላላቸው ሰዎች ምሳሌ እንድሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ዋና በምሆን በእኔ ላይ ትእግስቱን ሁሉ ያሳይ ዘንድ ምሕረትን አገኘሁ።”</u>፩ጢሞ፡፩፡፲፮።

ከዚህ በላይ በሰማነው ቃለ እግዚአብሔር በመመራት ያሳለፍነው ዓመት በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊው ሕይወታችን ላይ ድክመት ስንፍናና ሀኬት ዝለትና ውድቀት አሳይቶ ከሆነ በተሰጠን በአዲሱ ዓመት መንፈሣዊው ሕይዎታችን ጠንክሮ ሥጋዊው ሕይወታችን ካላስፈላጊ ምኞትና ትዕቢት ተላቆ በልዩ ልዩ ችግር የሚገኙ ወገኖቻችን በመርዳትና በማስረዳት እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትን ሥራ በመሥራት ከእዚአብሔር ጋር መኖር እንችል ዘንድ በትጋትና በንቃት ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ ለሰውም ለእግዚአብሔርም ከማይመች ተግባር እንራቅ፡፡

**<u>የፍቅር አባት የሰላም መሪ በንጹሕ ፍቅሩ የጠራችሁና ያከበራችሁ በሙሉ!</u>**

ዘመነ ማርቆስ የሰላምና የፍቅር የጤናና የብልጽግና የዕዉቀትና የሥራ የአንድነትና የሕብረት ዘመን እንዲሆንልን ፈቃደ እግዚአብሔር ይሁን እያልኩ በድጋሜ እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሳችሁ "ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከክርስቶስ ኢየሱስም ከጌታችን ጸጋና ምሕረት ሰላምም ይሁን"።

እግዚአብሔር አምላካችን ለሀገራችን ለኢትዮጵያና

ለዓለም ሁሉ ሰላምን ይስጥ

ይችን የምንኖርባትን አገር ምድረ አሜሪካንን በረድኤት ይጠብቅልን

አባ አብርሃም

የዋሽንግተን ዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከት

ሊቀጳጳስ

ስልክ/Telephone: 703-360-0105 www.eotcdc.org ፋክስ/Fax: 703-780-0850
አድራሻ/Address: 4210 Corcoran St. Alexandria, VA 22309 ወይም/or P.O. Box 77363 Washington, DC 20013-7363